
**MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION**
**ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት**

8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910
Tel: (202)-677-0094 Fax:
Web: http//www.moreshwegenie.org/

# በቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ዞን በሚኖሩ ዐማሮች ላይ የተፈፀመ የዘር ማጥፋት ወንጀል




ካርታ፡- የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ወረዳዎች

## በዐማሮች ላይ የተፈፀመ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ልዩ ዘገባ

ቅፅ ፫፣ ቁጥር ፩

ማክሰኞ ነሐሴ ፲፯ ቀን ፪ሺህ፲፬ ዓ.ም.

# ለመስማትም ሆነ ለማውራት ይዘገንናል!!

# በምን ቋንቋ እንግለጸው! ሰውን ሰው በላው!

# ጉምዞች ዐማሮችን አርደው በሏቸው!

## ሀ) መግቢያ

ሞረሽ-ወገኔ ይህ አስደንጋጭ ዜና እንደደረሰው የድርጊቱን ዘግናኝነት እና ፍፁም ኢሰብዓዊነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ ከዚያም አልፎ ያለአግባብ ግለሰቦችንም ሆነ ድርጅቶችን ላለመወንጀል፣ ስለሁኔታው ከሥር መሠረቱ መረጃዎችን ለማጣራት ሙከራ አድርጓል። ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን እና ሰብዓዊነት የሚሰማችሁ ግለሰቦች ሁሉ እንድትገነዘቡልን የምንፈልገው፣ በእንዲህ ዓይነት እጅግ የሚሠቀጥጥ ድርጊት ላይ ዘገባ ለማዘጋጀት ምን ያህል ከባድ የኅሊና ፈተና እንደሚደቅን ንፁሕ ኅሊና እና አስተዋይ አዕምሮ ያለው ሰው ይስተዋል አልባልም።

አንዳንድ ጊዜ «ቋንቋ ኃሣብን በትክክል ለመግለጽ ያስቸግራል» ይባላል። ዕውነት ነው፣ እንደዚህ ያለ ለመስማትም ሆነ ለመናገርም የሚቀፍ እና የሚከብድን ድርጊት፣ ድርጊቱን ባየው ሰው፣ በተረዳው እና በገባው መልክ ለሁለተኛ እና ለሦስተኛ ወገን ለመግለጽ ይቸገራል። የቋንቋ ሊቃውንቱም «ቋንቋ አንዳንድ ጊዜ ኃሣብን በትክክል አይገልጽም» የሚሉት እንደዚህ ያሉ ድርጊቶችን በአዕምሯቸው በተቀረጸው መንገድ በቃላት አሳክቶ ለመግለጽ ሲፈልጉ ተስማሚ ቃል ስለሚያጡ ነው። በዚህ በምንኖርበት በ፳፩ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ያውም የክርስትና ኃይማኖትን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ተቀብሎ በኖረ እንደ ኢትዮጵያ ባለ የረጅም ዘመን ታሪክ ባለቤት በሆነ ሕዝብ መሃል፣ «ሰውን ሰው በላው፣» «ጉምዝ የተባለው ጎሣ አባሎች የዐማራውን ነገድ አባሎች በጠላትነት ስሜት ተነሳስተው ከወያኔ በተሰጣቸው መመሪያ መሠረት አርደው በሏቸው» የሚለውን ክፉ ዜና ላልሰሙና ላላወቁ ሰዎች ማስረዳት እጅግ ይከብዳል፣ ይቀፋል፣ በምን ቃላትም ለመግለጽ እንደሚቻል ያስቸግራል። ድርጊቱ ግን በአሳዛኝ መልኩ ተፈጽሟል። በዕውነትም አንበሣ፣ ጅብ ወይም ሌሎች ሥጋ-በል አራዊት በመሰሎቻቸው ላይ የማይፈጽሙትን ድርጊት፣ ሰው ፣ሰውን አርዶ በሚጥሚጣ አጣጥሞ ሲበላው ላየ ሰው፣ ለሌላ ወገኑ ለመግለጽ ቃላት ያጥረዋል። የአገላለጽ መንገዱም ይጠፋዋል፤ ይከብደዋል። «ሰው ሰውን በላው» ማለት ተራ አባባል ይሆናል፤ የተለመደ ተራ አጠቃቀም ይሆናል። በምን ቃል ቢገለጽ ነው ድርጊቱ «ትንግርት፣ ጉድ፣ እግዚኦ የፈጣሪ ያለህ» የሚያሰኘው! ይህ ነው እንግዲህ «አንዳንድ ጊዜ ቋንቋ ኃሣብን በትክክል ለመግለጽ አያስችልም» የሚባለው። የሰው ልጅ ከጅብ እና ከአንበሣ፤ በአጠቃላይ ሥጋ- በል ከሆኑ እንስሶች የከፋ አውሬ መሆኑ እንዴት ይገለጻል?

ይህ አረመኔያዊ እና ኢሰብአዊ ድርጊት በዘመኑ ቴክኖሎጂ በቪዲዮ ተቀርፆ ለሕዝብ ዕይታ ቢቀርብ፣ ከቃላቱ ይልቅ ድርጊቱን እያንዳንዱ ተመልካች ዐይቶ የየራሱን ግንዛቤ እንዲጨብጥ ባስቻለ ነበር። ሆኖም ግን ምን ያደርጋል! ድርጊቱ የተከናወነበት አካባቢ እልም ያለ ገጠር እና ከዘመኑ የቴክኖሎጂ ትሩፋቶች የራቀ ከመሆኑም በላይ፣ ግድያ የተፈጸመባቸው ምስኪን ለፍቶ አዳሪ፣ ድሃ ገበሬዎች ናቸው። በሥፍራው ይህን ድርጊት ለብዙኃን የመገናኛ ዘዴዎች ለማቅረብ የሚችሉ፣ የዚህ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች የሉም። ከሁሉም በላይ ድርጊቱ የተፈጸመው በዐማራው ላይ በመሆኑ፣ ሁሉም «በወደቀ ግንድ ምሣር ይበዛበታል» ሆኖ፣ ጉምዞች ዐማሮችን አርደው በሉ! የሚለው ዘግናኝ ለጆሮ የሚከብድ፣ ለሕሊና የሚቀፍን አሳዛኝ ድርጊት በወቅቱ ለሕዝብ ሳይገለጽ አራት ወራት አስቆጠረ።

የትግሬ-ወያኔዎች፣ ገና ደደቢት በረሃ ሲገቡ ጀምረው፣ ዐማራውን በዘር ጠላትነት ፈርጀው፣ ዘሩን ለማጥፋት ሣይታክቱ ሠርተዋል። ከ፵(አርባ) ዓመታት በላይ በፈጀ ጊዜ ውስጥ ከ፭(አምሥት) ሚሊዮን በላይ ዐማሮችን ከምድረ-ኢትዮጵያ አጥፍተዋል። ከፍተኛ የሆነ የዘር ማጥፋት እና የዘር ማጽዳት ወንጀል ፈጽመዋል። የትግሬ-ወያኔዎች ዐማራውን ከመግደል፣ ከማሠር፣ ከማሰቃየት፣ ከሥራ ከማባረር፣ ስደተኛ እና ርሃብተኛ፣ ታማሚ እና ሟች ከማድረጋቸውም በላይ፣ በቅርቡ ደግሞ የሰው አውሬ የሆኑትን ጉምዞችን አደራጅተው፣ ዐማሮችን አርደው እና ከትፈው ሥጋቸውን እንዲበሉ አስደርገዋል። ስለዚህ ባለፉት አራት ወራት ጉምዞች መተከል ውስጥ ያደረጉት ዐማሮችን ገድለው ሥጋቸውን ከትፈው የመብላት የከፋ እርምጃ፣ ዘረኛው የትግሬ-ወያኔ አገዛዝ በዐማራው ላይ የገነባው የዘር ጥላቻ የቱን ያህል የከፋ እና የጠለቀ እንደሆነ ሌላው ማሣያ ሆኖ በታሪክ የሚመዘገብ ነው።

ይህ አስደንጋጭ እና አሣዛኝ መረጃ እንደደረሰን ለማጣራት የሞከርነው፦- የድርጊቱ መንስኤ ምንድን እንደሆነ፤ ድርጊቱ መቼ እና ዬት እንደተፈጸመ፤ የድርጊቱ ፈጻሚዎች እነማን እንደሆኑ እና ማን አመራር እንደሰጠ፤ የተጎጂዎቹ ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ፤ የደረሰባቸው ጉዳት መጠን እና ዓይነት፤ ከዚህ ጭፍጨፋ ከሞት ቢተርፉም ለወደፊት ለአደጋ የተጋለጡት ሰዎች ምን ያህል እንደሆኑ በሚሉት ላይ ነው። እነኚህን ጥያቄዎች ለመረጃ ምንጮቻችን ስናቀርብላቸው፣ ያለምንም ማመንታት ሕይዎታቸውን ለአደጋ አጋልጠው አስፈላጊውን ትብብር አድርገውልናል። መጠነኛ ዝርዝር ያዘለው ዘገባ እነሆ፥

## ለ) የድርጊቱ መነሻ

ጉዳዩ እንዲህ ነው፤ ኢትዮጵያውያን ዜጎችን በመግደል፣ በማሠር፣ በማጭበርበር እና ድምፅ በመስረቅ «በሕዝብ ተመረጥኩ» እያለ ለ፳፭(ሃያ አምሥት) ዓመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ የተፈናጠጠው የትግሬ-ወያኔ፣ የ፪ሺህ፯ ዓ.ም.ን አገር አቀፍ ምርጫ መቶ በመቶ ለማሸነፍ ባለው እኩይ ዓላማ እና ፍላጎት መሠረት፣ ይህኑ ፍላጎቱን ለማሟላት በመሣሪያነት የሚያገለግሉትን የልዩ ፖሊስ ኃይል ወደ መተከል ያሠማራል። የተላኩት የልዩ ፖሊስ ኃይል ሠራዊት የተሰጣቸውን እኩይ ተልዕኮ ለማሳካት የወሰዱት የመጀመሪያ እርምጃ፣ በቡለን እና በወምበራ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩትን ዐማሮች ሰብስቦ ማሠር እንዲሆን ወሰኑ። ዐማሮችን ለማሠር የሰጡት ምክንያትም፣ «ዐማራዎቹ በርካታ የጦር መሣሪያዎች ያሉዋቸው ስለሆነ፣ ምርጫውን እንዳያደናቅፉ በቁጥጥር ሥር ሆነው መቆየታቸው አስፈላጊ ነው፤» የሚል ነበር። ይህን በሐሰት ላይ የተመሠረተ ምክንያት በመስጠት፣ በሁለቱ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩትን ዐማሮች ሰብስበው አሠሩ። ሰብስበው ካሠሩ በኋላ፣ «መሣሪያ ደብቃችኋል እና አምጡ» በማለት ከፍተኛ የሆነ ድብደባ ፈጸሙባቸው። የተደበቀ መሣሪያ ባለመኖሩ የሚገኝ ሲጠፋ፣ በዚህ የተናደዱት ባለሥልጣኖች «በ፪ሺህ፬ ዓ.ም. በክልሉ የነበሩትን ዐማሮች ሰብስበን በአባረርን ጊዜ ጉዳዩን የብዙኃን መገናኛ ተቋሞች "በዐማራው ላይ የዘር ማጽዳት ወንጀል ተፈጸመበት" እያሉ በማናፈሳቸው፣ ክልሉ እንዲጋለጥ በመደረጉ ችግር ተፈጥሮብናል። ዛሬ እንደዚያ አይደረግም። የሚደረገው ዐማሮቹን እየለቀምን ባሉበት መጨፍጨፍ ነው። ለዚህም የወረዳ እና የቀበሌ ባለሥልጣኖች ኃላፊነቱን ወስደው መመሪያውን እንዲያስፈጽሙ፤» የሚል ትዕዛዝ አስተላለፉ።

ይህ መመሪያ በተላለፈበት እና ወደ ተግባር ለመለወጥ ሠፊ ዝግጅት እና ቅስቀሳ በሚደረግበት ወቅት፣ ማን እንደገደለው፣ መቼ እንደተገደለ፣ እንዴት እንደተገደለ በቅጡ የማይታወቅ የጉምዝ ጎሣ አባል የሆነ አንድ ሰው ወንበራ ወረዳ ውስጥ ሞቶ ተገኘ ተባለ። ይህን ሆን ተብሎ ዐማራን ለመጨፍጨፍ የተቀነባበረውን ሤራ ዕውነት ለማስመሰል፣ ባለሥልጣኖቹ የቡለን እና የወንበራ ወረዳ ነዋሪዎችን በየነገዳቸው ተለይተው እንዲሰባሰቡ ያዝዛሉ። በትዕዛዙም መሠረት የሁለቱ ወረዳ ነዋሪዎች ልዩ ልዩ ነገዶች በየነገዳቸው ተሰበሰቡ። ባለሥልጣኖቹ የዐማራው ነገድ አባሎች የሆኑት ወደ ተሰበሰቡበት ቦታ በመሄድ፣ «ጉምዙን የገደለውን ሰው አውጡ» ብለው አፋጥጠው ያዟቸው። ዐማራዎቹ ሲሞትም ሆነ ሲገደል ያዩት፣ የሰሙት እና የሚያውቁት ነገር ባለመኖሩ ሁሉም «አናውቅም» የሚል መልስ በአንድነት ሰጡ። በዐማሮቹ መልስ የተበሳጩት ባለሥልጣኖች፣ በቀበሌ ደረጃ ላሉት የጉምዝ ነገድ ባለሥልጣኖች «ዐማሮቹ በግድ ገዳዩን ለይተው እንዲያወጡ አድርጉ፤» ብለው ትዕዛዝ ሰጥተው ወደመጡበት ተመለሱ። ከዚያ በኋላ የተከሰተው ድርጊት ለመናገርም ሆነ ለመዘገብ እጅግ የሚዘገንን፣ በእኛ ዘመን የተፈፀመ፣ ዳግማዊ ኦሽዊትዝ የታዬበት ነው።

## ሐ) ዳግማዊ ኦሽዊትዝ በመልካን እና አይጋሊ-ሞዛምቢክ ቀበሌዎች

ትዕዛዙን የተቀበሉት በወምበራ ወረዳ የመልካን የቀበሌ ባለሥልጣኖች ግንቦት ፳ እና ፱ ቀን ፪ሺህ፯ ዓ.ም. ሰብስበው በአሠሯቸው፣ እንዲሁም በየቤታቸው በሚገኙ ሕፃናት፣ አዛውንት፣ ሴቶች፣ ነፍሰጡሮች እና አቅመ ደካማ ዐማሮች ላይ አሰቃቂ ግድያ ፈጸሙባቸው። ፋሽስት ጣሊያን በየካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በአዲስ አበባ ነዋሪዎች ላይ እንዳደረገው፣ ጉምዞችም ዐማሮችን በገጀራ፣ በቢለዋ፣ በአካፋ እና በዶማ ቀጥቅጠው ገደሏቸው። በእነዚህ ሁለት ቀኖች ብቻ ከ160 በላይ ዐማሮች የገና ጠቦት ሆኑ። ከመዓቱ ሩጦ ለማምለጥ ሙከራ ያደረጉትን ጥይት ቀድሞ ቀለባቸው፤ በመተከል ጫካዎች ወደቁ። በየቤታቸው የነበሩትን ትንሽም ሆነ ትልቅ፣ አዋቂም ሆነ ሕፃን፣ ደካማ እና እርጉዝ ሳይለዩ አረዷቸው። ዐማሮች ይተኙበት የነበረው መደብ እና አልጋ በደም ጨቀየ። ይመገቡባቸው የነበሩት ሣህን እና ሌማቶች የእነርሱው ሥጋ ተበልቶ የገዳዮቹ የጉምዞች የኩራት ምግብ ሆነ። የዐማሮችን ኩላሊት እና ጉበት ከትፈው በሚጥሚጣ ለውሰው እንደ ዱለት በሉት። የዐማሮች ሥጋ እንደ በሬ ሻኛ እና ደቢት ተቆጥሮ ቁርጥ ሆኖ ተበላ። የሰው ልጅ አስከሬን መቀበሪያው መሬት ሳይሆን የጉምዞች ሆድ ሆነ። «የሰዉ ሥጋ እርም ነዉ፤» የሚለው የቆዬ ብሂል በጉምዞች ሠፈር እና ባህል ተረት መሆኑን ይህ ድርጊት ያስረዳል።

ነፍሰጡር ዐማሮች ሆዳቸው በሳንጃ ተሰነጠቀ፤ በጭንቀትም አስወረዱ። በማኅፀን ውስጥ ያሉት ሽሎች በጉምዞች ቢለዋ ተበጣጥሰው ተጣሉ። «የሰው ልጅ ከእናቱ ማኅፀን ሲወጣ ምን ይመስላል» በማለት ሆድ ቀደው ሽል ተመለከቱ። የዐማራው እናቶች እና እህቶች የጉምዞች መጫዎቻ አሻንጉሊት ሆኑ! ብቻ በዚህ ቦታ እና በዚያ ሰዓት የተገኘ ዐማራ ጉምዞች የሰከረ ዓሣ እንዳገኙ ከተፉት። ትምህርት ቤት ያሉ ተማሪዎች እንኳ ከመታረድ አላመለጡም። ጉምዞቹ የገደሏቸውን የወንዶች ዐማሮችን ብልት ቆርጠው የወንድነት (የጀግንነት) መለኪያ እና መሸለሚያ አደረጉት። የሙታኑን ክንዶች እና መዳፎች እየቆረጡ ለከበሮ መምቻ አደረጉት። ወይ ነዶ!

በባህላችን አባቶቻችን እና እናቶቻችን «አሟሟቴን አሳምረው» የሚሉት፣ እንዲህ ዓይነቱ ሞት እንዳይገጥማቸው ነው። በመልካን ቀበሌ ለዘመናት ይኖሩ የነበሩት ዐማሮች አሟሟታቸው አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን፣ እጅግ አሠቃቂ እና ዘግናኝም ነው። ከመበላት እና ከመዘልዘል የተረፈው የተገዳዮች ዐማሮች ተረፈ-አካላት፣ በአቅራቢያው ወዳለው ወደ ‹ጉርሻ ወንዝ› ተጣሉ። የአባወራ ቤቶች ከእነአስከሬኖቻቸዉ እየሸተቱ ለሣምንታት ተዘጉ። እስካሁንም ድረስ በመልካን ቀበሌ የተገደለ አንድም የዐማራ አስከሬን አልተቀበረም።

ከአንድ ወር በኋላ፣ ማለትም፥ ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ሺህ፯ ዓ.ም. እንደገና መላዕከ-ሞት ወደ ቡለን ወረዳ ‹አይጋሊ-ሞዛምቢግ› ቀበሌ ዘመተ። በትግሬ ወያኔዎች «ጃዝ» ባይነት የተበረታቱት የጉምዝ ጎሣ አባሎች፣ ሁለት ዐማሮችን አረዱ፤ በተመሳሳይ ሁኔታም

ኩላሊታቸዉን እና ጉበታቸዉን እንደ ዱለት በሚጥሚጣ እያጣቀሱ በሉት። በኢጋጣሚም ይሁን የፈጣሪ ኃይል ተጨምሮበት፣ ሁለቱን ዐማሮች የገደሉት እና የበሉት ጉምዞች በፖሊሶች ተያዙ። በሰዓቱ የቡለን ወረዳ መርማሪ ፖሊስ የነበረችዉ አንዲት ‹የኦሮሞ› ነገድ ተወላጅ የሆነች ሴት፣ በምርመራዉ ወቅት ገዳዮቹ እንዴት ድርጊቱን እንደፈጸሙ ስትጠይቃቸዉ ሁለቱን ዐማሮች እንዴት አድርገዉ እንደገደሏቸዉ፣ ሥጋቸዉንም እየበለቱ እንዴት እንደበሉት ሲነግሯት ከመስማት በላይ ሆነባት እና ወዲያውኑ ኅሊናዋ ታውኮ አስታወካት። «ኤሎሄ፣ ኤሎሄ፣ ላማ ሰበቅታኒ!!!» የሚባለው በእንዲህ ዓይነቱ ዘመን ነው።

ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ቀበሌዎች ውስጥ በጉምዞች በከፍተኛ ጭካኔ ከታረዱት እና ከተገደሉት 162 ዐማሮች መካከል ስማቸውን ለማግኘት የቻልናቸውን የ፹፰(ሰማንያ ስምንቱን) በሚከተለው **ሠንጠረዥ ፩** ቀርቧል።

## ሠንጠረዥ ፩፡- በመልካን ቀበሌ (ወምበራ ወረዳ) እና በአይጋሊ-ሞዛምቢክ ቀበሌ (ቡለን ወረዳ) በግፍ የተጨፈጨፉ ዐማሮች ከፊል ዝርዝር

| ተ.ቁ | የሟች ስም (የታረደዉ ሰዉ ስም) | አብሮ የታረደ የቤተሰብ ብዛት | ወረዳ (ቀበሌ) | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዋለልኝ ገረመዉ | | ወምበራ (መልካን) | የአብዛኞቹ ሟቾች አካል ቅሪት ወደ ጉርሻ ወንዝ ተጥሏል። ስንቱ አስከሬን ወደ ወንዝ እንደተጣለ እና ስንቱም አካል እንደተበላ በክልሉ መንግስት በከፍተኛ ምሥጢር ተይዟል። መረጃውን ያቀበሉን ግለሰቦች እንደገለጹልን፣ የአካባቢው ፖሊስ 30 ሰዎች መሞታቸዉን ብቻ እንዳመነ ተናግረዋል። |
| 2 | አለሙ ካሣ | 4 | ወምበራ (መልካን) | |
| 3 | መልኩ ቢተዉ | 2 | ወምበራ (መልካን) | |
| 4 | አለምየ አበበ | 4 | ወምበራ (መልካን) | |
| 5 | በቀለ አበበ | 3 | ወምበራ (መልካን) | |
| 6 | ካሴ አበበ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 7 | ሙላት ታደሠ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 8 | ደምሴ ዋለልኝ | 6 | ወምበራ (መልካን) | |
| 9 | ደመቀ ታደሠ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 10 | ንብረት መለሠ | 5 | ወምበራ (መልካን) | |
| 11 | ቻሌ መንግሥት | 1 | ወምበራ (መልካን) | |
| 12 | ሽፈራው ወርቄ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 13 | አለሙ ጥላየ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 14 | ወይዘሮ ጥሩነሽ ጥላየ | 3 | ወምበራ (መልካን) | |
| 15 | ወይዘሮ ይርገዱ ጥላዬ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 16 | ወይዘሮ ፈለጉሽ ካሳዬ | 4 | ወምበራ (መልካን) | |
| 17 | ጌታሁን ደባሱ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 18 | አብተዉ ወሌ | 3 | ወምበራ (መልካን) | |
| 19 | ተማሪ አዲሴ ወሌ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 20 | ተማሪ ከንድነህ ወሌ | | ወምበራ (መልካን) | |

## ሠንጠረዥ ፩፡- (የቀጠለ)

| ተ.ቁ | የሟች ስም<br>(የታረደዉ ሰዉ ስም) | አብሮ የታረደ የቤተሰብ ብዛት | ወረዳ (ቀበሌ) | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 21 | ወይዘሮ ከበቡሽ ግርማ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 22 | አያሌዉ ጌታሁን | 4 | ወምበራ (መልካን) | |
| 23 | ደረጀ አዳሙ | 5 | ወምበራ (መልካን) | |
| 24 | ጠሀይነህ አዳሙ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 25 | ዋሲሁን ግርማ | 5 | ወምበራ (መልካን) | |
| 26 | የሻንበል ዘመነ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 27 | ይትባረክ መላኩ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 28 | አጥናፍ አለሙ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 29 | መለሠ ሁነኛዉ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 30 | ወርቅነህ ተፈራ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 31 | ደሣለዉ ባያብል | | ወምበራ (መልካን) | |
| 32 | ወለላዉ ሥዩም | | ወምበራ (መልካን) | |
| 33 | ገረመዉ ፈንቴ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 34 | ሙሉነህ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 35 | ብሬ ሰለሞን | | ወምበራ (መልካን) | |
| 36 | ወረኛዉ ዘለቀ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 37 | መሸሻ ደሣለኝ | | ወምበራ (መልካን) | |
| 38 | ጋሻው ፋንታሁን | | ቡለን (አይጋሊ) | የሁለቱም ዐማሮች ኩላሊት እና ጉበት ተበልቷል። የራስ ቅላቸዉም ሜዳ ቀርቷል፡፡ |
| 39 | ታከለ ብዙዓለም | | ቡለን (አይጋሊ) | |
| | **አጠቃላይ ድምር** | **88 ሰዎች** | | |

## መ) በሕይዎት በተረፉት ዐማሮች ላይ ያንዣበቡ አደጋዎች

በአሁኑ ጊዜ በወምበራ ወረዳ ባሉ አንዳንድ ቀበሌዎች የጉምዝ እና የሽናሻ ጎሣዎች አባሎች ዐማራን ሙሉ በሙሉ ጨርሰዋል፤ የተረፉትንም አሰድደዋል። በቡለን ወረዳ ያሉት ዐማሮችም ከያሉበት እየተያዙ ታስረዋል። ነፍሰ ጡሮች ‹በዶቢ እና ባሮዳ› እየተደበደቡ ነዉ። በአካባቢው ያሉት የጉምዝ ፖሊሶች እና ሚሊሺያዎች «አይበቁም» ተብሎ፣ ፳፰(ሃያ ስምንት) የሚሆኑ የልዩ ኃይል ፖሊሶች ዐማራን ለመፍጀት ወደ ቡለን ዘምተዋል። በቅርብ ቀን እንኳን ነሐሴ ፰ ቀን ፪ሺ፱፺ ዓ.ም. አንድ «መንግስቱ ተባባል» የሚባልን ግለሰብ ልብሱን አውልቀው፣ መለመላዉን (ራቁቱን) አድርገው፣ ገርፈዉ፣ ሲደክም ዶቢ ቀበሌ ለመቀጣጫ እንዲሆን ብለው መንገድ ላይ ጥለውት ሄደዋል። ለድብደባው እና ለመቀጣጫነት እንዲሆን የሰጡት ምክንያት፡- «በዐማራው ነገድ ላይ እየተደረገ ያለውን ፍጅት ለዉጭ ሰዉ ተናግሯል» የሚል ነው።

በኢትዮጵያ ከሰኔ ወር ጀምሮ እስከ መኸር ድረስ ዋናው የእርሻ ወቅት መሆኑ ይታወቃል። ገበሬው የዓመት ጉርሱን፣ የዕዳ መክፈያ እና ለከፈኑ የሚሆነውን ሰብል የሚዘራው እና የሚኮተኩተው በሰኔ እና በሐምሌ ወሮች ውስጥ ነው። ሆኖም ይህ መሆኑ እየታወቀ ከሰኔ ፲፪ ቀን ፪ሺ፱፰ ዓ.ም. ጀምሮ የቡለን ወረዳ ነዋሪ የሆኑ በርካታዎቹ ዐማሮች ሕይዎታቸዉን ለማትረፍ ሲሉ ቤት ንብረታቸውን ጥለው፣ ኑሯቸዉን ከዱር አራዊት ጋር በጫካ ውስጥ አድርገዋል። ከብቶቻቸውን፣ በጎቻቸውን እና ፍየሎቻቸውን አባራሪዎቻቸው ጉምዞች እና ሽናሻዎች የግላቸው አድርገዋቸዋል። በዐማራው ላይ እንኳን በንብረቱ፣ በሕይዎቱ ሣይቀር አዛዡ የትግሬ-ወያኔ የሾመው የየነጡ ምሥለኔ ከሆነ ፳፰(ሃያ አምሥት) ዓመታት ተቆጥረዋል።

በደረሱን መረጃዎች መሠረት በአሁኑ ወቅት ከ224 በላይ ቤተሰቦች እና አባዎራዎች በየጫካው ተበትነው የአውሬ እራት ከመሆን ወይም በጉምዝ-ሽናሻ ታጣቂዎች ከመገደል፣ ከሁለት ዓይነት ሞቶች አንዱን በመምረጥ አስቸጋሪ አጣብቂኝ ውስጥ ይገኛሉ። ጫካ ውስጥ የተደበቁት እና በቡለን ወረዳ ነዋሪ የሆኑት ዐማሮች እንደ መልካን ቀበሌ (ወምበራ ወረዳ) ዐማሮች ሁሉ ሊገደሉ እየታደኑ ነዉ። እነህ ወገኖች የድረሱልኝ ጥሪያቸዉን እያሰሙ ናቸዉ። ከዚህ ከተደቀነባቸው ዕልቂት ሊታደጋቸው የሚችል ማን ይሆን? ሕይዎታቸዉ ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጦ የድረሱልን ጥሪ ከሚያሰሙት መካከል የከፊሉ ስም በሠንጠረዥ ፪ ተዘርዝሯል።

**ሠንጠረዥ ፪፡- በዶቢ እና ጭላንቆ ቀበሌዎች (ቡለን ወረዳ) ተፈናቅለው በጫካ የተጠለሉት ዐማሮች ስም ዝርዝር**

| ተ.ቁ | የተፈናቃዩ ስም | የቤተሰብ ብዛት | ወረዳ (ቀበሌ) |
|---|---|---|---|
| 1 | መልኬ ዘገየ | 10 | ቡለን (ዶቢ) |
| 2 | ቻሌ መልኬ | 7 | ቡለን (ዶቢ) |
| 3 | እጅጉ ይስማዉ | 11 | ቡለን (ዶቢ) |
| 4 | ስንታየሁ እጅጉ | 3 | ቡለን (ዶቢ) |
| 5 | በለጠ ሙሉ | 5 | ቡለን (ዶቢ) |
| 6 | ተዋቸዉ ጋሹ | 3 | ቡለን (ዶቢ) |
| 7 | ንብረቱ መለሰ | 8 | ቡለን (ዶቢ) |
| 8 | ውድነኅ ዘገየ | 5 | ቡለን (ዶቢ) |
| 9 | ግርማዉ ዘገየ | 4 | ቡለን (ዶቢ) |
| 10 | መልካሙ መላኩ | 5 | ቡለን (ዶቢ) |
| 11 | ሰዋረግ አዳሙ | 8 | ቡለን (ዶቢ) |
| 12 | መልሰዉ ሰዋረግ | 2 | ቡለን (ዶቢ) |
| 13 | ማተቤ ሙሉነህ | 3 | ቡለን (ዶቢ) |
| 14 | አስተዉል አያሌዉ | 5 | ቡለን (ዶቢ) |
| 15 | አበበ አለባቸዉ | 3 | ቡለን (ዶቢ) |
| 16 | እንደሻው ታረቀኝ | 2 | ቡለን (ዶቢ) |
| 17 | አድኅ ገደፋዉ | 5 | ቡለን (ዶቢ) |
| 18 | አሰፋ ጥላሁን | 3 | ቡለን (ዶቢ) |
| 19 | ንበረት ይልማዉ | 4 | ቡለን (ዶቢ) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 20 | ስሜነህ ንብረት | 2 | ቡለን (ዶቢ) |
| 21 | ገረሜ እጅጉ | 2 | ቡለን (ዶቢ) |
| 22 | አለምነህ ወለላዉ | 5 | ቡለን (ዶቢ) |
| 23 | ውለታዉ እንደሻዉ | 4 | ቡለን (ዶቢ) |
| 24 | ደሴ እንደሻው | 5 | ቡለን (ዶቢ) |
| 25 | ቀለሙ ታየ | 7 | ቡለን (ዶቢ) |
| 26 | መልካሙ ታዬ | 3 | ቡለን (ዶቢ) |
| 27 | ካሣ ተፈራ | 7 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 28 | አበበ ካሴ | 2 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 29 | ገዳሙ ሙሉ | 12 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 30 | መልካሙ አበጀ | 7 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 31 | ነጋሽ አበጀ | 6 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 32 | ጫኔ ጥላሁን | 7 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 33 | ደሴ ገዳም | 5 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 34 | ጌታነህ ገዳም | 4 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 35 | ነጋ አስፋዉ | 6 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 36 | በሬ ጋሸው | 4 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 37 | ሙሉአለም አበበ | 4 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 38 | መንግስቱ እውነቱ | 3 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 39 | ቻሌ አቤ | 4 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 40 | ባዜ ቸኮል | 5 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 41 | ደሴ አቤ | 8 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 42 | አድምጤ ቀለሜ | 3 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 43 | ዋሴ አዲስ | 6 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 44 | ጌጤ አዱኛ | 2 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 45 | ተፈራ አድማስ | 3 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| 46 | ሽቴ | 2 | ቡለን (ጭላንቆ) |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **224** | |

## ሠ) ያለፉ ድርጊቶች ዋቢነት

ባለፉት ፳፭(ሃያ አምሥት) ዓመታት በቤንሻንጉል-ጉምዝ ክልል በሚኖሩ ዐማሮች ላይ ጉልቆ-መሣፍርት የሌለው ግፍ ሲፈፀም ቆይቷል። በቅርብ ዓመታት እንኳን፦ በ፪ሺህ፬፣ ፪ሺህ፭ እና ፪ሺህ፮ ዓ.ም. በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ዐማሮች በግፍ እና በገፍ የዘር ማጽዳት ዘመቻ ተካሂዶባቸዋል፣ በሺህዎች የሚቆጠሩት ደግሞ በዘር ማጥፋት ድርጊት በጅምላ መፈጀታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። በዐማራው ላይ ይህ ሁሉ ግፍ የሚፈጸመው በትግሬ-ወያኔ አጋፋሪነት መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። የትግሬ-ወያኔዎች ባለፉት ፳፭(ሃያ አምሥት) ዓመታት ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ፭ ሚሊዮን የማያንሱ ዐማሮችን በተለያዩ ዘዴዎች ማጥፋታቸውን የተለያዩ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እና ታዋቂ ምሁራን ከራሳቸው ከወያኔዎች የመረጃ ምንጮች ላይ በመነሳት ባደረጉት ጥናት አረጋግጠዋል። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዐማሮች ከሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች በዘር ማጽዳት ዘመቻ መፈናቀላቸው ይታወቃል። ስለዚህ ሠሞኑን ከወደ መተከል (ቤንሻንጉል-ጉሙዝ) የሰማነው የዳግማይ-ኦሽዊትዝ ሠቆቃ የትግሬ-ወያኔ በዐማራ ሕዝብ ላይ የሚፈጽመው ተከታታይ ትራጄዲ አንድ አካል መሆኑ እሙን ነው።

## ረ) ይድረስ ለመላው የዐማራ ነገድ ተወላጆች፦ ከትዝብት ይልቅ የተግባር እርምጃ ያስፈልጋል

«ኢትዮጵያ» በሚባል ሠፊ ውቅያኖስ ውስጥ ሆነህ፣ አብሮህ የሚርመሰመሰው ሻርክ እና ዓሣ ነባሪው ቆርጥሞ እየጨረሰህ ነው። በአሁኑ ዘመን ውቅናኖሱ ውስጥ ያሉት «ሁሉም ፍጥረቶች» በሚባልበት ደረጃ ያንተ ጠላቶች ሆነዋል። በሠፊው ውቅያኖስ ውስጥ በሰላም መኖር የምትችለው በውስጡ የሚኖሩት ፍጥረቶች ሁሉ ያንተን ኀልውና አውቀው እንደነሱ የመኖር መብትህን ሲያከብሩልህ ብቻ ነው። ይህን ማረጋገጫ የምታገኘው ደግሞ በመፍራት እና በመሸሽ ሳይሆን፣ ተደራጅተህ መብትህን እና ጥቅምህን ለማስከበር ዝግጁ ስትሆን ነው። ተደራጅተህ በቡድን እና በተናጠል የሚያጠፉህን እና ሊያጠፉህ የተነሱትን «አልጠፋም! እምቢኝ! አሻፈረኝ!» ልትላቸው ይገባል። አለያ ከዚህ በፊት ከምድረ-ገፅ እንደጠፉት ነገዶች ታሪክ ብቻ ሆነህ ትቀራለህ፤ ታሪክህንም ጠብቆ የሚያቆይልህ ከተገኘ። ስለሆነም ራስህን እና ተተኪውን የዐማራ ትውልድ ለማዳን የሚደረገው ይህ ተልዕኮ ለነገ በይደር ቀጠሮ የሚያዝ አይደለም። ከላይ በሪፖርቱ እንደተጠቀሰው መተከል ዞን፣ ቡለን ወረዳ ውስጥ በጭንቅ ላይ ሆነው የ«ድረሱልን» ጥሪ የሚያሰሙት ወገኖችህ ጊዜ የላቸውም። በመሆኑም ዛሬውኑ ለጥሪያቸው ይህን መረጃ ባስተላለፈው የዐማራው ድምፅ ለሆነው ሞረሽ ወገኔ «ምን ልርዳ? ከእኔስ ምን ይጠበቃል?» ብለህ ጠይቅ። የምትረዳበትን መንገድ ያመላክቱሃል። አሁን ወደ ተግባር የምንገባበት እንጂ፣ ጉንጭ አልፋ ለሆነ ሙግት አጀንዳ የምንከፍትበት ወቅት ላይ አይደለንም። እንነሣ! ለጥሪው አዎንታዊ መልስ እንስጥ!

**በሞት አፋፍ ላይ ሆናችሁ የ«ድረሱልን» ጥሪ ለምታሰሙት የዐማራው ነገድ አባሎች፦** «ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይደርስም፤ ለስለት የሰጡት ገላ ቢቆርጡት አይደማም» እናም በድንጋይ፣ በጦር፣ በቆመጥ፣ በበርበሬ፣ በአጠቃላይ በእጃችሁ ባለው በማንኛውም መሣሪያ ተጠቅማችሁ፣ እንደገና ጠቦት ሊያርዷችሁ ከአሰፈሰፉት ጠላቶቻችን ጋር ተናንቃችሁ የክብር ሞት ለመሞት ቆርጣችሁ በአንድነት ተነሱ። እንኳን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ይቅሩና፣ አንድ ሰው ሲሸፍት አገር ያስቸግራል። የዚህን ጊዜ ድምፃችሁ ይሰማል፤ አጋዦቻችሁ ከየትም ይደርሳል። ስለዚህ በዚህ ረገድ ዕወቁበት። ዛሬ ለመኖር መዳዳት ያለባቸው በቅምጥል ሕይዎት ውስጥ የሚፍነሸነሹት የትግሬ-ወያኔ ቡድን እና ሆድ አደሮቻቸው እንጂ፣ እናንተ ለምኑ ዳጉታችሁ የማይቀረውን ሞት በቁማችሁ ሞታችሁ ትጠብቁታላችሁ! አኩሪና ታሪካዊ ሞት ለመሞት እንዘጋጅ! እንቁረጥ!

**ለአዲሱ ወጣት የዐማራ ትውልድ፦** በታሪካችን የአባትን፣ የወንድምን፣ የወገንን ገዳይ እስከ ሰባት ትውልድ እየተከታተሉ ደም መመለስ የጀግንነት እና የኩራት መለያ መታወቂያችን ነበር። ዛሬስ? ታሪክ ዋሸ? ወይስ ትውልድ ተኮላሸ? ኧረ ጎበዝ ይህ ድርጊት የዐማራውን ወጣት አስቆጥቶ ለመብቱ እና ለነፃነቱ ቆርጦ ለመታገል ካላስወሰነ፣ የአባት እና የወንድሙን ደም እንዲመልስ ካላስሸፈተ፣ ወያኔን «አለሁ-ብህ! መጣሁ!» ካላለ፣ ዐማራው ዘሩ ፈጽሞ ማለቁ የማይቀር መሆኑን መናገር ክፉ ህልም አላሚ መሆን አይደለም።

ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደግ!

ሞት ለዐማራው ጠላቶች!